*4127 Redwood Road*
*Oakland, CA 94610*
*Tel: (510) 530 - 3681*

መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም

*ቍጥር፣170/99*

**«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን።**

**ከሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ «የትንሣኤው ምስክሮች እነ ማን ናቸው» ? በሚል ርእስ የወጣ ቃለ ቡራኬ።**

የተወደዳችሁ በሀገር ውስጥ በገዳማትና በአድባራት የምትገኙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በዓለም ዙሪያ ያላችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን በሙሉ፣ ቸርነቱ የማያልቅበት ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ፥ በረድኤቱም መግቦ፥ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ።

«አማን ተንሥአ እግዚእነ ወአስተርአዮ ለስምዖን» ጌታ በእውነት ተነሥቷል፣ለስምዖንም ታይቶታል» እያሉ ትንሣኤውን ሲመሰክሩ፥ ስለ ትንሣኤውም ሲነጋገሩ አገኙአቸው። (**ሉቃስ** 24፥34)

## <u>የትንሣኤው ምስክሮች እነ ማን ናቸው?</u>

<u>**የተወደዳችሁ ካህናትና ምእመናን !**</u>

**ለመሆኑ እነዚህ የትንሣኤው ምስክሮች እነማን ናቸው?**

<u>**የትንሣኤው ምስክሮች፣**</u>

ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የመሰከሩ፥ አሁንም እየመሰከሩ ያሉ፥ ወደ ፊትም እስከ ዕለተ ምጽአት የሚመሰክሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው። ቅዱሳት መጻሕፍት የትንሣኤው ምስክሮች መሆናቸውንም የተናገረ ጌታ ራሱ ነው፤ እንዲህ ይላል፣«እርሱም እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፥ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና፥ ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው፣ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ፥ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው» ይላል። (**ሉቃስ** 24፥25)
በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን ምስክሮች በዝርዝር እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

<u>**የነቢያት ምስክርነት በብሉይ ኪዳን፤**</u>

አሁን እንዳየነው፥ የትንሣኤው ምስክሮች ነቢያት ናቸው፤ ብለናልና፥ ስለ ጌታ ትንሣኤ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ምሳሌ ተመስሏል፥ ትንቢትም ተነግሯል።

<u>ሀ. ምሳሌ</u>፣ የነቢዩ የዮናስ ታሪክ ለክርስቶስ ትንሣኤ ምሳሌ ነበር። ቃሉም እንዲህ ይላል፤ « እግዚአብሔር ዮናስን የሚውጥ ታላቅ ዓሣ አሰናዳ፣ ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ነበረ፤ ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ፥ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤....

እግዚአብሔርም ዓሣውን አዘዘው፤ እርሱም ዮናስን በየብስ ላይ ተፋው» ይላል። (ዮናስ 2፥1-11)

ይህም የዮናስ አስገራሚ የሕይወት ታሪክ፥ለትንሣኤው ትክክለኛ ምሳሌ በመሆኑ፥ ጌታችን ራሱ፥ አንጻራዊ ምሳሌ አድርጎ፥ለትንሣኤው ምስክር ጠቅሶ አስተምሮታል። ቃሉም የሚከተለው ነው፣«እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፣ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፣ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በስተቀር፥ ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፤ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ፥ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ይኖራል» ብሏል። ((ማቴ 12፥38) ዮናስ የጌታ ምሳሌ ሲሆን፥ ከርሠ አንበሪ ደግሞ፥ የከርሠ መቃብር ምሳሌ ነው።

## ለ. ትንቢት፤

ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ትንቢት ከተናገሩት ነቢያት አንዱ፥ቅዱስ ዳዊት ነው፣ስለ ክርስቶስ መከራ ሲናገር፥ እንዲህ ይላል። «አገቱኒ ከለባት ብዙኃን፣ ወአኃዙኒ ማኅበሮሙ ለእኩያን፣ ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ፣ ወኖለቊ ኲሎ አእጽምትየ፣እሙንቱሰ ጠይቆሙ ወተአወሩኒ፤ ወተካፈሉ አልባስየ ለርእሶሙ፣ ወተአጸዉ ዲበ አራዝየ» ይህ ወደ አማርኛ ሲተረጎም፥ብዙ ውሾች ከብበውኛል፥ የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ፥እጆቼን እግሮቼን ቸነከሩኝ፣አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፣እነርሱም አዩኝ፥ተመለከቱኝም፤ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ በቀሚሴም ላይ እጣ ተጣጣሉ» ማለት ነው። (መዝ 21፥16 )

ዳዊት ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ቀድሞ የነበረ፥ በእሥራኤል ላይ የነገሠ ታላቅ ሰው ነበረ። ዳዊት በጠላት ተይዞ አያውቅም ነበር፤ዳዊት እጆቹ እግሮቹ አልተቸነከሩም ነበር።ዳዊት አጥንቶቹ አልተቆጠሩም፣ ልብሶቹንም አልተገፈፈም። በዳዊት ቀሚስ ላይ እጣ አልተጣለም። ባጠቃላይ፥ ያዙኝ፥ ቸነከሩኝ፥አጥንቶቼን ቆጠሩ። እጣ ተጣጣሉብኝ ብሎ የተናገረው ስለ ጌታ መከራ፥ስለ ጌታ ሞት፥በመሆኑ፥ ይህ ዳዊት የተናገረውን ትንቢት በዕለተ ዐርብ በጌታችን ላይ፥ አንድ በአንድ አይሁድ እንደ ፈጸሙበት አራቱም ወንጌላውያን ጽፈውታል። ይህ ብቻ አይደለም፣ «ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ፣ ወአስተዩኒ ብሒአ ለጽምእየ» ለመብሌ ሐሞት ሰጡኝ፣ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ» ብሏል። (መዝ 68፥21)

ጌታ በመስቀል ላይ ሁኖ ተጠማሁ ባለ ጊዜ፥ መራራ ሐሞት ሲአጠጡት፥ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ አንድ ሺህ ዓመት ቀድሞ የተነገረ የዳዊት ትንቢት ተፈጸመ። ዳዊት መከራውን፥ ሞቱን ብቻ ተናግሮ አልቀረም። ሙስና መቃብርን አጥፍቶ፥በፍጹም ትንሣኤ በኃይል፥ በሥልጣን መነሣቱንም እንደሚከተለው ተናግሯል። «እስመ ኢተኃድጋ ውስተ ሲኦል ለነፍስየ፣ ወኢትሁቦ ለጻድቅከ ይርአይ ሙስና» <u>ነፍሴን በሲኦል አትተ ዋትምና</u> ፣ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም» ይላል። (መዝ 15፥8-11)

ይህንም ዳዊት ስለ ክርስቶስ እንደ ተናገረው፥ መንፈስ ቅዱስ የገለጠለት ቅዱስ ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ትምህርቱ እንዴት እንደ ተረጎመው ቀጥሎ እንመልከት። «ወንድሞች ሆይ ስለ አባቶች አለቃ ስለ ዳዊት እንደ ሞተም፥እንደ ተቀበረም፥ ለእናንተ በግልጥ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ። መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው። ነቢይ ስለሆነ፥ ከወገቡም ፍሬ በዙፋኑ ያስቀምጥ ዘንድ፥ እግዚአብሔር መሐላ እንደ ማለለት ስላወቀ፥ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ፥ ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች፥ ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ፤ ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው፣ ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን» (የሐዋ 2፥29)

ቅዱስ ዳዊት በዚህ ብቻ አላበቃም፤ ሞትን ድል ነሥቶ፥ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ፥ መነሣቱን እንደሚከ ተለው ይገልጠዋል። «ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃህ እምንዋም፣ ወከመ ኃያል ወኅዳገ ወይን፣ ወቀተለ ጸሮ በድኅሬሁ» እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ። የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው፣ ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ» (መዝ 77፥66)

ይህም ማለት የተኛ እንዲነሣ፥እንዲሁ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ፥ፍጹም አምላክ ሲሆን፥ በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ነውና፤ በለበሰው ሥጋ ከአይሁድ የደረሰበትን ጸዋትወ መከራ ተቀብሎ፥በመስቀል ተሰቅሎ፥

ሙቶ፥ተቀብሮ፥ሙስና መቃብርን አጥፍቶ፥ዓለምን አድኖ፥እነሣለሁ እንዳለ፥በሦስተኛው ቀን ፈጥኖ ተነሣ። ጠላቶቹን አጋንንትንም በኋላቸው መታ። ማለት ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ተነሥቶ፥ ለአዳም ለሔዋን ፈረደላቸው። በጠላት ዲያብሎስ ላይ ግን ፈረደበት ማለት ነው።

## የትንሣኤው ምስክሮች በሐዲስ ኪዳን፣

1ኛ. ጌታ፤ ጌታ ራሱ ከሞቱ አስቀድሞ፥ በመዋዕለ ትምህርቱ፥እሞታለሁ፥ እነሣለሁ ብሎ፥ ለደቀ መዛሙርቱ ብዙ ጊዜ አስተምሮአል። ትምህርቱም በምሳሌም በቀጥታም ነበር፤ ከዕለታት አንድ ቀን፥ አይሁድ፥ ይህን ስለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ? ቢሉት፥« ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ» አላቸው። (ዮሐ 2፥18)

ጌታ መቅደስ ያለው ሰውነቱን ነበር። እነርሱ ግን ምሳሌው ስላልገባቸው፥ይህ ቤተ መቅደስ ሥራው አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቷል። አንተ ግን በሦስት ቀን አነሣዋለሁ ትላለህ። ብለው፥ ለጊዜው ተሳልቀውበታል። ኋላ ግን በዕለተ ዐርብ፥ ለማሰቀል ካቀረቡበት አራት የክስ ነጥቦች አንዱ ይህ ነበረ። በመሆኑም የሐሰት ምስክሮች፥ ጥንቱን በምሳሌ የተሰጠው ትምህርት፥ ሳይገባቸው፥ ያውም ደግሞ፥ጌታ ያላለውን፥ ጨምረው አጋንነው፥በሐሰት እንደሚከተለው መስክረውበታል። «ሰዎችም ተነሥተው፥ እኔ ይህን በእጅ የተሠራውን ቤተ መቅደስ አፈርሰዋለሁ። በሦስት ቀንም ሌላውን በእጅ ያልተሠራውን እሠራለሁ፣ ሲል ሰማነው። ብለው፥በሐሰት መሰከሩበት።ምስክርነታቸውም እንዲሁ እንኳ አልተስማማም። (ማር 14፥58)

ከዚህ በላይ የተመለከትነው፥ጌታ ትንሣኤውን በቤተ መቅደሱ መስሎ የተናገረውን ነበር። አሁን ደግሞ በቀጥታ እንበለ ምሳሌ፥ እነሣለሁ እንዳለ እንመልከት። «እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፣ ስለ ሰው ልጅም፥በነቢያት የተጻፈው ይፈጸማል። ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፣ይዘብቱበትማል፣ ያንገላቱትማል፣ ይተፉበትማል፣ ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል። በሦስተኛውም ቀን ይነሣል» (ሉቃስ 18፥31)

አይሁድም እነሣለሁ ማለቱን ጠንቅቀው ያውቁ ነበርና፥ትዝ ብሏቸው፥ዮሴፍና፥ኒቆዲሞስ ከቀበሩት በኋላ፥ «በማግስቱም ከመዘጋጀት በኋላ በሚሆነው ቀን፥ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን፥ ወደ ጲላጦስ ተሰበሰቡና፥ ጌታ ሆይ፥ ያ፥አሳች፥ በሕይወቱ ገና ሳለ፥ ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ፤ እንዳለ ትዝ አለን። እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው፥ በሌሊት እንዳይሰርቁት፥ ለሕዝቡም ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ፥ የኋለኛዪቱ ስህተት፥ ከፊተኛዪቱ የከፋች ትሆናለችና ፤ መቃብሩ እስከ ሦስተኛ ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት። ጲላጦስም ጠባቆች አሏችሁ፣ ሂዳችሁ እንዳወቃችሁ አስጠብቁ አላቸው። እነርሱም ሂደው ከጠባቆች ጋር፥ድንጋዩን አትመው፥መቃብሩን አስጠበቁ» ይላል። (ማቴ 27፥62)

ነቢዩ ሕዝቅኤል በምዕራፍ 44 ላይ በተናገረው መሠረት፥መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታተመ ማሕፀን እንደ ተወለደ፥ እንዲሁ ሲነሣም መቃብር ክፈቱልኝ፥ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል፥ መቃብሩ እንደ ተዘጋ፥ እንደተቆለፈ፥ እንደ ታተመ፥ተነሣ። በዚህ ጊዜ ነቢያት የተናገሩት ትንቢት፥የመሰሉት ምሳሌ ተፈጸመ። ራሱ ጌታም «ነፍሴን ደግሞ፥አነሣት ዘንድ አኖራለሁ። ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጅ፥ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፥ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ» ብሎ የተናገረውም ተፈጸመ። (ዮሐ 10፥17)

እስካሁን ያየነው ስለ ትንሣኤው የነቢያትንና የጌታን ምስክርነት ነበር። አሁን ደግሞ የምናየው የቅዱሳት አንስትን፥ የመላእክትንና የደቀ መዛሙርቱን ምስክርነት ነው።

## 2ኛ. የቅዱሳት አንስት ምስክርነት፣

ቅዱሳት አንስት አንድም፥ ሁለትም፥ሦስትም እየሆኑ፥በአይሁድ ባሕል መሠረት፥ሽቱ ሊቀቡ እሑድ ማለዳ እጅግ ማልደው፥ ወደ መቃብሩ ሲሄዱ፥ ሁሉም ያሰቡ የነበረው የመቃብሩን ድንጋይ ማን ያንከባልልናል፤ የሚል ነበር። ወደ መቃብሩ በደረሱ ጊዜ፥ከማቴዎስ በቀር በሦስቱም ወንጌላውያን እንደምንረዳው፥ሁሉም፥ ድንጋዩ ተንከባልሎ፥መቃብሩም ተከፍቶ፥ተመለከቱ።ሁሉም ይፈሩ ስለ ነበር፥መላእክት ተገልጠው፥እናንተስ አትፍሩ፣ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን እንድትሹ እናውቃለን። ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን

ትፈልጋላችሁ? ብለው መቃብሩን አሳዩአቸው። እነሆ መቃብሩም ባዶ ነበር። በማቴዎስ ወንጌል ግን ለየት ያለ የተብራራ ምስክርነት እናገኛለን። አሁንም ሴቶች ስለ መቃብሩድንጋይ እያሰቡ፥ከመቃብሩ ደርሰው ሳለ፥ ዘበኞችም መቃብሩን እየጠበቁ ሳለ፥ አንድ አስደናቂ ነገርበድንገት ተከሰተ። ታሪኩም የሚከተለው ነው።

## 3ኛ. የመልአኩ ምስክርነት፤

«እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ፥ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ። ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ፣ መልኩም እንደ መብረቅ፥ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ።

« ወእምግርማሁ ተሀውኩ እለ የአቅቡ መቃብረ፤ ወኮኑ ከመ አብድንት። ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ፤ እንደ ሞቱም ሆኑ» ይልና፣ለሴቶቹ ግን « መልአኩም ሴቶቹን አላቸው፤ እናንተስ አትፍሩ፣የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤እርሱ፥እነሣለሁ ብሎ እንደ ተናገረ፥ተነሥቷል፤ በዚህ የለም። የተኛበትን፥ማለትም የተቀበረበትን ስፍራ ኑና እዩ፥አላቸው። ሴቶቹም መቃብሩን አይተው የመልአኩን ግርማውንና የነገራቸውን እያደነቁ፥የጌታን ሥጋውን አግኝተው፥ሽቱ ባለመቅባታቸው፥ ባጠቃላይ ስለ ሁኔታው እያዘኑ፥ እያደነቁም ፈጥነው ሲሄዱ ሳለ፥እነሆ ከመንገድ ጌታ ኢየሱስ አገኛቸው፤ ደስ ይበላችሁ አላቸው፤እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት። ጌታ ኢየሱስም አትፍሩ፣ሂዱችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሯቸው አላቸው።

## ትንሣኤውን ለማስተባበል የተደረገ የአይሁድ ካህናት ክፉ ምክር፣

መቃብር ጠባቂ ዘበኞችም ወደ ከተማ መጥተው፥ የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ። የካህናት አለቆች ግን ይህን ሲሰሙ ዝም አላሉም፤ ከሽማግሌዎች ጋር ተሰብስበው ተማከሩ፤ ለጭፍሮችም ማለትም፥ለመቃብር ጠባቂ ዘበኞች ብዙ ገንዘብ ሰጥተው፥ እኛ ተኝተን ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ፤ ይህም በገዥው ዘንድ የተሰማ እንደሆነ፥ እኛ እናስረዳዋለን። እናንተም ያለ ስጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሏቸው። እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንዳስተማሩአቸው አደረጉ። ገንዘብ፥ጥቅም፥ዓይነ ልቡና ያሳውራል፥ የተነሣውን አልተነሣም፤ያልተሰረቀውን ተሰረቀ፥ ብለው አወሩ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል። (ማቴ 28፥11-15)

## የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን !

እኛ ግን ነቢያት በመሰከሩት፥ ጌታችን ባስተማረው፥መላእክት በመሰከሩት፥ቅዱሳት አንስት በመሰከሩት፥ ቅዱሳን ሐዋርያት በመሰከሩት፥ ባጠቃላይ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ተነሣ ብለው በመሰከሩት መሠረት፥ « በአማን ተንሥአ ክርስቶስ እምነ ሙታን» ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤያችን በኩር ሆኖ በእውነት ተነሥቷል። ብለን እናምናለን። ቤተ ክርስቲያንም እንዲህ እያለች ትዘምራለች።

«ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን፥ በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን፥ አሰሮ ለሰይጣን፥ አግአዞ ለአዳም፥ ሰላም፥ እም ይእዜሰ ይኩን ሰላም» ክርስቶስ ተነሣ ከሙታን፥ በታላቅ ኃይልና በታላቅ ሥልጣን፥ ሰይጣንን አሰረው፥ አዳምን ነጻ አወጣው፤ ሰላም ከእንግዲህስ ይሁን ሰላም»

## 4ኛ. የሐዋርያት ምስክርነት፤

በአራቱም ወንጌላውያን እንደ ተጻፈው፥ ቅዱሳት አንስት መላእክት የነገሩአቸውን፥ በዐይናቸውም በመቃብሩ የተመለከቱትንና ያዩትን ሁሉ፥ ለደቀ መዛሙርቱ ነገሯቸው። እነርሱ ግን የነገሯቸውን ከማድነቅና፥ ነገሩምን ይሆን? ከማለት በስተቀር ገና ትንሣኤውን ሙሉ በሙሉ አላመኑም ነበር። ሁኖም ግን አይሁድን ከመፍራት የተነሣ፥ ደጆቹን አጥብቀው ዘግተው፥ ሁኔታውን በመጠባበቅና በመጨዋወት ላይ ሳሉ፥ ክብር ይግባውና፥ ሞትን መቃብርን፥ ድል አድርጎ የተነሣው፥ የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው ቆሞ፥ ሰላም ለእናንተ ይሁን ብሎ፥ ሰላም ላጡት ደቀ መዛሙርቱ፥ ሰላምን ሰበከላቸው። ትንሣኤው እውነት እንደሆነ ለማጠየቅም፥ የተወጋ ጐኑን፥ የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን፥ አሳያቸው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን ሲመሰክር እንዲህ ይላል። «እርሱን እግዚብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው። ይገለጥም ዘንድ ሰጠው። ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን፥ለእኛ ነው እንጅ። ይልና፥በመቀጠል፥ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ፥ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣን እኛ ነን። ለሕዝብም እንድንሰብክ፥ በሕያዋን በሙታን ሊፈርድ፥ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደሆነ፥እንመሰክር ዘንድ አዘዘን።በእርሱ የሚያምን ሁሉ፥በስሙ የኃጢአቱን ሥርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል» አለ። (**የሐዋ** 10፥40)

ቅዱስ ጴጥሮስ በ1ኛ መልእክቱ፥ በሞቱ በትንሣኤው የተገኘውን ዋና ነገር፥ እንዲህ ይገልጠዋል። «ሞተ በሥጋ፥ወሐይወ በመንፈስ፣ ወሖረ ኃበ እለ ሙቅህታ ትነብር ነፍሶሙ፣ ወሰበከ ሎሙ ግእዛነ» «በሥጋ ሞተ፥ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ። በእርሱም ደግሞ ሂዶ፥ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት፥ ነጻነትን ሰበከላቸው» (**1ኛ ጴጥ** 3፥18)

በዚህ ዓለም ሥርዓት እንኳ አንድ ንጉሥ ከጠላት ሀገር ገብቶ መስበክ የሚችለው፥እስረኞችን መፍታት ምርኮኞችን ነጻ ማውጣት የሚችለው፥ በአጠቃላይ በጠላት ሀገር ላይ የፈለገውን ማድረግ የሚችለው፥ መጀመሪያ ሠራዊቱን ደምስሶ፥ጠላቱን ገድሎ፥ወይም ማርኮ፥የጠላቱን ሀገር ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠረና ድል ካደረገ በኋላ ነው።

« አልቦ ዘይክል በዊአ ቤተ ኃያል፥ ወበርብሮተ ንዋዩ፥ ለእመ ኢቀደመ አሲሮቶ ለኃያል፥ ወእምዝ ይበረብር ቤቶ። « ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር፥ ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ፥ እቃውን ሊነጥቀው፥ ቤቱንስ ሊዘርፈው እንዴት ይችላል? ይችላልን? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል» እንዳለ ጌታ በወንጌል። (**ማቴ** 12፥29)

ሞት የማይገባው፥ በመለኮቱ ፈጽሞ ሞት የሌለበት፥ በመንግሥቱ ሽረት፥ በባሕርዩ ኅልፈት፥ ውላጤ የሌለበት ሲሆን፥በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ስለሆነ፥በለበሰው ሥጋ፥ስለ እኛ በመስቀል ሙቷልና። «ሞተ በሥጋ» አለ፤ ቅዱስ ጴጥሮስ። ከዚህ ላይ ይጠነቀቋል። ሞቱ የሥጋና የነፍስ መለያየት ነው። መለኮታዊ አካለ ቃል ግን ከሥጋ ጋር በመቃብር፥ከነፍስ ጋር በሲኦል ነበር እንጅ፥ከሥጋም ከነፍስም ለቅጽበትስ እንኳ አልተለየም። በሞቱ ሞትን ድል ነሣ፤ በመቀበሩም ሙስና መቃብርን፥ማለት በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አጠፋ። በሲኦልም ለነፍሳት ነጻነትን ሰበከ አለ። ነጻነትን ሰበከላቸው ማለትም ከአዳም ጀምሮ፥ እስከዚያ ቀን ድረስ፥ አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን በሲኦል ተግዘው፥ ታስረው፥ በእግረ አጋንንት ተረግጠው ለነበሩ ነፍሳት፥ «እለ ውስተ ሲኦል ጻኡ፥ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ፥ ወርእዩ ብረሃነ ዐቢየ» በሲኦል ያላችሁ ውጡ፣ በጨለማም ያላችሁ ተገለጡ፥ ታላቅ ብርሃንንም እዩ፣ ተመልከቱ፤ ብሎ ነጻነትን ሰበከላቸው ማለት ነው። (ኢሳ 49፥9) በዚህ ጊዜ፥ በሲኦል ያሉ፥ ነፍሳት፥ እንደ ንብ ከላዩ ላይ ሰፍረው ይዟቸው ወጥቷል» ድል ማድረጉ በምን ይታወቃል ቢሉ፥ በትንሣኤው ይታወቃል። በሦስተኛው ቀን መነሣቱ ድል ቢያደርግ ነውና።

ስለዚህ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በዓለ ትንሣኤውን በየዓመቱ ስታከብር ሁለት ዋና ዋና ነጥቦችን በማሰብ ነው። ይኸውም፥

1. ጌታ ሞትን መቃብርን ድል አድርጎ መነሣቱን በማሰብ ነው። ድሉ ድሏ ነውና።
2. በጌታ ሞትና ትንሣኤ ያገኘችውን ነጻነት ለማዘከር ነው።

በአጠቃላይ ትንሣኤው ለቤተ ክርስቲያን <u>የድል</u>ም፥ <u>የነጻነት</u>ም በዓል ስለሆነ፥ በየዓመቱ በከፍተኛ ድምቀት ስታከብረው ትኖራለች።

<u>የተወደዳችሁ ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ !!!</u>

ሰላም ለእናንተ ይሁን !

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ፥ ለደቀ መዛሙርቱ በአንድነት ሳሉ ሲገለጥላቸው፥

ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገረው ቃል፥ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» ብሎ ነው። በኃዘን የተቀጠቀጠው፥ የደቀ መዛሙርቱ ልቡና በዚህ በመድኃኒታችን ሰላም ተፈወሰ። ኃዘናቸው ወደ ደስታ ተለወጠ። ትንሣኤውንም በሙሉ ልባቸው አምነው ተቀበሉ።

ዛሬ በዓለም ሰላምን በማጣት፥ በፍርሃት፥ በጭንቀት፥ በር የተዘጋባቸው ስንቶች ናቸው? በጦርነት ምክንያት ሰላም አጥተው፥ ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ፥ በድርቅ በረኃብ ምክንያት ሰላም አጥተው፥ እንደ ቅጠል የሚረግፉ፥ በአስከፊ በሽታ ምክንያት፥ሰላም ያጡ ስንቶች ናቸው? ባጠቃላይ በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ ችግር ምክንያት ሰላም ያጡ፥ ተስፋ የቆረጡ፥ በእስር ቤት የሚማቅቁ፥ አጥር የታጠረባቸው፥ በር የተዘጋባቸው፥ ስንቶች ናቸው?

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን !

እኛም በበኩላችን በዓለ ትንሣኤውን ስናከብር፥ በሰው ሠራሽም ይሁን በተፈጥሮ፥ ብቻ በማናቸውም ምክንያት ሰላም ያጣውን፥ ያዘነውን፥ የተራበውን፥ የተሰደደውን፥ በሞትና በሕይወት መካከል ያለውን፥ በሀገራችን በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ያለውን ወገናችንን ሁሉ፥ በጸሎትም፥ በገንዘብም በመደገፍና የችግሩ ተሳታፊ በመሆን፥ የትንሣኤው ምስክሮች መሆን ይገባናል።

እንዲህ የሆነ እንደሆነ፥ ፋሲካን ማክበር ትክክልኛ ትርጉሙን ያገኛል። የበዓለ ትንሣኤው አከባበር ትክክለኛ ትርጉሙም ይኸው ነው።

የታተመ መቃብር የማያስቀረው፥ መቃብር ጠባቂ ዘበኞች የማይቆጣጠሩት፥ የተቆለፈ፥የተዘጋ በር የማይከለክለው፥ ይህን ሁሉ አልፎ፥ ወደ ውስጥ ገብቶ፥ በፍርሃት በጭንቀት፥ ለነበሩ ሐዋርያት፥ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» ብሎ ትንሣኤውን የመሰከረ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ዛሬም፥ ሰላም ከእርሱ ነውና፥እርሱ በሚያውቀው መንገድ፥ለሀገራችን ለኢትዮጵያ፥ለዚህች ላለንባት ሀገር ለአሜሪካ በር ለተዘጋባቸው በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የሰው ልጆች ሁሉ፥ ከእርሱ ዘንድ ሰላም ይሁንላቸው።

በዓለ ትንሣኤው የሰላም የፍቅር፥የበረከት በዓል ይሁንልን።

ልዑል እግዚአብሔር ይባርካችሁ።
በትንሣኤውም ብርሃን ልቡናችሁን ያብራ!!!

አሜን።

**ከሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን**
**ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት፤**

**መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም**